# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## <u>ዜና ዘገባ</u>

**ሚያዚያ 27 ቀን 2005 ዓ.ም**

**የቤንሻንጉለል ጉሙዝ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ከስልጣኑ ሊነሳ ይችላል ተባለ፤**

**ሶማሊያ ያለውን ጦር አስመለክቶ የወያኔ ባለስልጣናት የቃረነ መግለጫ ሰጡ**

**ወያኔ ጦርም ከሱማሊያ እየወጣ መሆኑ ተነገረ፤**

**በእነ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ላይ ተፈርዶ የነበረው ህገ ወጥ ፍርድ እንዲፀና ተደረገ**

በቅርቡ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከ20 ዓመታት በላይ የኖሩ የአማራ ተወላጆች በግፍ መፈናቀላቸውን ተከትሎ ከየአቅጣጫው የተነሳውን ተቃውሞ ተከትሎ ወያኔ .በዞንና በወረዳ አስተዳዳሪዎች ላይ የቅጣት እርምጃ እወስዳለሁ በማለት በይፋ እየተናገረ ቢሆንም ይህ የፈጸሙትን የዘር ማጥፋት ወንጀል ለመሸፋፈን ነው ሲሉ መላው የሀገሪቱ ዜጎች በቁጭት እና በንዴት እየገለጹ ይገኛሉ፡፡

የወያኔ ቡድን በተለይ ባለስልጣናት በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ርዕሰ መስተዳድር እና በዞንና በወረዳ ባለስልጣናት ላይ የጥቃት በትር ለማሳረፍ ዝግጅት ማድረግ መጀመራቸውን ከፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር አከባቢ የተገኘው ዜና ገልጿል፡፡

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አህመድ ናስርና የክልሉ የዞንና የወረዳ ባለስልጣናት ለተፈናቀሉት እና ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች ተጠያቂወ ናችሁ ተብለው ግምገማ የተቀመጡ ቢሆንም የወያኔ ባለስልጣበናት እንዳሰቡት እየሄደላቸው እንዳልሆነም ከደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

አስገራሚው ነገር በሚኒስትር ማዕረግ የተቀመጠው የደኢህዴኑ ሽፈራው ተክለማርያም የተባለው ሰው በግምገማው ላይ እንዳይገኝ ተደርጎ ከሱ በታች ያሉት የመምሪያ ኃላፊ የሆኑ የወያኔ

ሰዎች  የክልሉን ፕሬዝዳንት ጨምሮ እስከ ወረዳ ድረስ ያሉትን ባለስልጣናት ለሶስት ቀናት በግምገማ ወጥረው የሰነበቱ መሆኑንም ይሄው የደረሰን ጥቆማ ገልጾዋል::

በዚሁ ተደረገ በተባለ ግምገማ ላይ ከተነሱት ዋነኛ አጀንዳ መሀከል የተሰጣችሁን ትዕዛዝ ቀስ በቀስ እና ደረጃ በደረጃ መውሰድ ሲገባችሁ በጅምላ መፈጸማችሁ  ለዓለም አቀፍ ውግዘት እና ለህዝብ ተቃውሞ መቀስቀስ ዋነኛ መንስዔ ሆናችሁዋል ስለሆነም ተጠያቂው እናንተ ናችሁና አምናችሁ ይቅርታ ጠይቁ በማለት የወያኔ ባለስልጣናት ጫና ሲያደርጉ ቢሞክሩም ስምምነት ላይ ሳይደረስ መቅረቱን ከስፍራው ያገኘነው ዜና ይገልጣል::

የክልሉ ፕሬዝዳንት አህመድ ናስር የተባለው ግለሰብ በበኩሉ እናንተ የሰጣችሁኝን ትዕዛዝ ተግባራዊ በማድረጌ ተጠያቂ አልሆንም ...ከስሬም ያሉት በፍጹም ሊጠየቁ አይገባም መጠየቅ ያለበት ሀሳቡን ያመጡት የላይኛው አመራር አባሎች ናቸው በማለት ስም ጠርቶ እንዳጋለጠም የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር ማሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ በተደረገ ግምገማ ጥፋቱ የላይኞቹ ባለስልጣናት መሆኑ እየታወቀ ወደ ክልል ባለስልጣናት ጣትን መቀሰር ተገቢ አይደለም ሲል ሲሞግት የሰነበተው አህመድ ናስር በህወሀቶቹ ባለስልጣናት ጥርስ ስለተነከሰበት ምናልባትም በቅርቡ  ከክልል ፕሬዝዳንትነቱ ሊነሳ ይችላል ተብሎ_እየተነገረ ይገኛል::

በተያያዘ ዜና ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ተፈናቅለው ፍኖተ ሰላም ሜዳ ላይ ተዘርግፈው የነበሩትና የበታች ሹማምንት የፈጸሙት ስህተት ነው ተብለው በግዳጅ ታፍሰው የተመለሱ የአማራ ብሔር ተወላጆች በአሁኑ ሰዓት በከፍተኛ ችግር ላይ እንደሚገኙ ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ ገለጸ::

የሀገሪቱን ሕዝቦች እና የዓለም አቀፉን ሕብረተሰብ ለማዘናጋት እና ለማታለል ተብሎ የተመለሱት ተፈናቃይ ዜጎች ወደ ነበሩበት ቀዬ እንዲመለሱ ቢደረጉም ሀብት ንብረታቸው ወድሞና ጠፍቶ ያገኙት ከመሆኑም በላይ የእለት ጉርስ የሚላስ የሚቀመስ አጥተው በከፍተኛ ችግር ላይ እንደሚገኙ ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ ገልፆዋል::

ዝርፊያ .....ድብደባ...... እስራትና እንግልት ሲደርስባቸው በጅምላ የነበሩበትን ቀዬ ጥለው ወጥተው የነበሩት ዜጎች በግዳጅ እንዲመለሱ ቢደረጉም በመጡበት ዕለት ብቻ ስምንት ኪሎ የፉርኖ ዱቄት ከተሰጣቸው በሁዋላ እስከ ዛሬ ዞር ብሎ ያያቸው ባለመኖሩ ለከፋ ርሀብ እና ስቃይ እንደተዳረጉና አሁንም ከስደት ኑሮ ባልተናነሰ በከፍተኛ ችግር ላይ ወድቀው እንደሚገኙ ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

ተፈናቃይ ዜጎች እንደሚሉት ከሆነ በግዳጅ ታፍሰን በጭነት መኪና ታሽገን እየተደበደብን ስንባረር ጎተራችን ሙሉ..... ሌማታችን ጭምር እርጥብ እንጀራ እውስጡ እንደነበር እንዳንወስደው ተከልክለን የነበረ ሲሆን አሁን ስንመጣ የደረቀው እንጀራ እንኳዋን በሌማቱ ውስጥ የሌለ ከመሆኑም በላይ አንድም ንብረት እንዳይተርፍ ተደርጎ በመዘረፉ በከፋ ችግር ላይ መውደቃችንን ለዓለም ሕብረተሰብ አሳውቁልን እያሉ ሲማጸኑ እንደነበር ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል::

አያይዘውም ከመፈናቀላችን በፊት አብረውን የነበሩት የክልሉ ተወላጆች በፍቅር እና በሰላም አንተ ትብስ አንቺ እየተባባልን የነበረ ሲሆን አሁን ግን ከተመለስን በሁዋላ ከእኛ ጋር እንዳይቀርቡና ማሕበራዊም ሆነ ማንኛውንም አይነት ግንኙነት እንዳይደርጉ በመከልከላቸው እነሱም እኛ ንም በአይነ ቁራኛ የሚከታተሉ ደህንነቶች መመደባቸውን በይፋ ተናግረዋል፡፡

በዚህም የተነሳ የአካባቢው ተወላጆች ሊረዱን የፈለጉትን ነገር እንዳይረዱን በመከልከላቸው እያዘኑና እያለቀሱ ከእኛው ጋር በከፍተኛ ችግር ውስጥ ይገኛሉ ሲሉም እነዚሁ ተፈናቃይ ዜጎች ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ በወያኔ ዓቃቤ ህጎችና እና በብአዴን ዳኞች መሀከል ሲያነታርክ እና ሲያጨቃጭቅ ብሎም ሲያወዛግብ የነበረው የእነ እስክንድር ነጋ የይግባኝ ውሳኔ በወያኔዎቹ የበላይነት መጠናቀቁ ታወቀ፡፡

በሀሰተኛ ማስረጃ በአገር ክህደት እና በአሸባሪነት ክስ ተመስርቶባቸው ከ14 ዓመት እስከ እድሜ ልክ ፍርድ የተወሰነባቸው በእነ እስክንድር ነጋ የይግባኝ ዙሪያ ንትርክ እና ውዝግብ ብሎም ትርምስ ሲካሄድ ቆይቶ ሐሙስ ሚያዝያ 24 ቀን 2005 ዓ.ም በነበረበት ሁኔታ እንዲቀጥል ውሳኔ መተላለፉ ታወቀ፡፡

ከወራት በፊት በከፍተኛ ፍርድ ቤት 4ኛ ወንጀል ችሎት የተወሰነባቸውን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ያሉት ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋና እነ አንዱዓለም አራጌ ያቀረቡት አቤቱታ አንዳችም ለውጥ ሳይደረግ የበታች ፍርድ ቤት የወሰነው ውሳኔ ተግባራዊ እንዲሆን ማጽናቱ ታውቆዋል፡፡

በህወሀት ዓቃቤ ህጎች እና በጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ አማረ አሞኘ መሀከል ውዝግብ እና ንትርክ ተፈጥሮ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩን እና የብአዴን ሊቀመንበር የሆነውን ደመቀ መኮንን ጨምሮ በሽምግልና ሲያሳትፍ የነበረው የሁለቱ ጎራ ፍልሚያ በህወሀቶቹ የበላይነት እና አሸናፊነት መጠናቀቁ ታውቆዋል፡፡

አማረ አሞኘ የተባለው የብአዴኑ ዳኛ ጉዳዩን መርምሮ አንዳችም ጥፋት አላገኘሁባቸውም ስለዚህ በነጻ ልለቃቸው ነው ብሎ በመናገሩ የተደናገጡት የወያኔ አቃቤ ህጎች ዘረኛ በማለት ጭምር ሰድበው አና አንጉዋጥጠው ጉዳዩን ወደ አለቆቻቸው በመውሰዳቸው በሁለቱ ቡድኖች የተፈጠረውን ውጥረት ለማርገብ ሲባል ፋይሉን ቀምተው ለዳኜ መላኩ የሰጡት ቢሆንም በእሱም በኩል ተመሳሳይ አቋዋም በመያዙ ሁኔታውን የትምህርት ሚኒስትሩ... ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ... የብአዴን ሊቀመንበሩ ደመቀ መኮንን ጣልቃ ገብቶ እንዲያስተካክል በህወሀቶች በተነገረው መሰረት መመሪያ ሰጥቶ የነበረ ሲሆን በተባለው መሰረት የወያኔ ዓቃቤ ህጎች አሸናፊ በመሆን ውሳኔው እንዲጸና መደረጉን ጉዳዩን ሲከታተሉ የነበሩ ወገኖች ገልጸዋል፡፡

እስረኞቹ በከፍተኛው ፍርድ ቤት የተወሰነብን ውሳኔ ያለአንዳች በቂ ማስረጃ በመሆኑ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ በነጻ እንዲያሰናብተን በማለት ይግባኝ ጠይቀው የነበረ መሆኑ የሚታወስ ሲሆን በከአምስት ግዜ በላይ በቀጠሮ ከተመላለሱ በሁዋላ ሐሙስ ዕለት ፍፃሜ ማግኘቱ ታውቆዋል፡፡

ዓቃቤ ህግ ያቀረባቸው የሰው ምስክሮቹም ሆነ የሰነድ ማስረጃዎቹ ድርጊቱን መፈጸማችሁን የሚያስረዳ ነው፤ የዓቃቤ ህጉን ማስረጃዎች የሚያስተባብሉና የሚያፈርስ ማስረጃ ባለማቅረባችሁ ያቀረባችሁት አቤቱታ ውድቅ ሆኖዋል በማለት ዳኜ መላኩ የተባለው የመሀል ዳኛው በንባብ ገልጾ ውሳኔውን አጽንቶ መዝገቡን መመለሱን ጉዳዩን በችሎት ሲከታተሉ የነበሩ ወገኖች ገልጸዋል::

የእነ ዳኜ መላኩ ችሎት በበላይ አለቆች በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት የሽብር ድርጊቶችን ለመፈጸም በማሴር.... በማቀድ...በማነሳሳት እና በማዘጋጀት ወንጀል በሚል ተከስሰው በከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ቅጣት ያጸና ሲሆን በዚህም መሰረት የአንድነት ፓርቲ አመራሩ አንዱዓለም አራጌ በእድሜ ልክ.....ናትናኤል መኮንን በ18 ዓመት.....ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ በ18 ዓመት.....ዮሐንስ ተረፈ በ13 ዓመት.....ሻምበል የሺዋስ ይሁን ዓለም በ15 ዓመት..... ክንፈሚካኤል ደበበ በ16 ዓመት ...አንዱዓለም አያሌው በ14 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ በማለት ውዋኔ ማሳለፉ ታውቆዋል::

ዳኜ መላኩ የተሰኘው የመሀል ዳኛ ውሳኔውን በንባብ አሰምቶ ፋይሉ ተዘግቶዋል ብሎ የመጨረሻውን ቃል እንዳሰማ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ **«ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር...እውነት ምን ግዜም ተደብቃ አትቀርም .....እውነቱ ይወጣል ...»**እያለ ድምጹን ከፍ አድርጎ መፈክር ሲያሰማ ባለቤቱ ጋዜጠኛ ሰርክአለም ፋሲል አይዞህ እኔም ሆንኩ የኢትዮጵያ ህዝብ ከጎንህ ነው ያለነው አይዞህ ስትል ያበረታታችው ሲሆን በችሎት የተገኘው ህዝብ ገሚሱ በጭብጨባ ሌላው በለቅሶ አጅቦዋቸው እንደነበር ችሎት ከተገኘው ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን የደረሰን ጥቆማ ገልጾዋል::

በሌላ ዜና ደቡብ አፍሪካ በአባይ ግድብ ስም ገንዘብ ለማሰባሰብ ሄዶ ተዋርዶ የተመለሰው የህወሀቱ ከፍተኛ ባለስልጣን ቲዎድሮስ አድሀኖም እና ተላላኪው የወያኔ ጉዳይ አስፈጻሚ ኃይለማርያም ደሳለኝ በየፊናቸው መግለጫ የሰጡበት ጉዳይ በወያኔ ባለስልጣናት መሀከል እያወዛገበ እንደሚገኝ ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ጥቆማ አጋለጠ::

ኃይለማርያም ደሳለኝ ጦሩን ከሱማሊያ ልናስወጣ ነው ብሎ ማክሰኞ ሚያዚያ 15 ቀን 2005 ዓ.ም ለተወካዮች ምክር ቤት ባቀረበው የ8 ወር ሪፖርት ላይ የሰጠውን መግለጫ በመፃረር የህወሀቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቲዎድሮስ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ስብሰባ ላይ ጦሩ እንደማይወጣ በመናገሩ በወያኔ ቡድን ውስጥ ንትርክ ፈጥሮ እንደሰነበተ ለማወቅ ተችሏል::

ቲዎድሮስ አድሀኖም ጠቅላይ ሚኒስተር ተብየውን መግለጫ በመጻረር ለመናገር ያበቃው በቅርቡ በወያኔዎቹ መከከል በነበረው ልዩነት ይህንን ለመናገር የልብ ልብ ያገኘው የበላይ ሆኖ ወጣ የተባለው የእነ አዜብ ቡድን ከጀርባው ስላለ ነው የሚል ግምት ያለ ሲሆን የሃይለ ማርያምን መግለጫ ተከትሎ ጦሩ ከሁሉም የሱማሌ ግዛት ወጥቶ በኢትዮጵያ ድንበር ላይ እንዲሰፍር መደረጉን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ አስረድቶዋል::

በሱማሊያ ገብቶ ያለው ጦር የአበል ክፍያ ጥያቄ ማንሳቱንና ሁዱር የተባለች የሱማሊያ ከተማን ለቅቆ ወደ ድንበር መጠጋቱን እንዲሁም ጦሩ ሙሉ ለሙሉ በቅርቡ ለቅቆ ሊወጣ በዝግጅት ላይ

መሆኑን ባለፈው ሳምንት መዘገባችን የሚታወስ ሲሆን ሰሞኑንም ከባይድዋና ከሌሎችም የሱማሌ ግዛቶች ጉዋዙን ሸክፎ መውጣቱ ተነግሮዋል፡፡

በመጨረሻም የሀገሪቱን መከላከያ ሚኒስትር በበላይነት በያዘው በህወሀት ጄኔራል መኮንኖች መሀከል በተደረገ ሽኩቻ ነባር መኮንኖች ተባርረው በአዳዲሶች እየተተኩ መሆናቸውን ከመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ለማወቅ ችለናል፡፡

በህወሀት ክፍፍል ወቅት ከእነ ጄኔራል ጻድቃን ገ/ተንሳይ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ነበራቸው የተባሉ የህወሀትና የብአዴን ጄኔራል መኮንኖችን በጡረታ እና በሕመም ሰበብ እያሰናበቱዋቸው ሲሆን በምትካቸው አዳዲስ የህወሀት ጄኔራሎች ተብየዎች ቦታቸውን እየያዙ መሆኑን ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

በቅርቡ በጡረታ ተሰናበተ በተባለው የህወሀት ነባር ታጋይ እና የመከላከያ ሎጀስቲክ ክፍል ኃላፊ በነበረው ገዛኢ አበራ ምትክ ለግዜው በሚል ዘውዱ እሸቲ የተባለው የጦር አለቃ መመደቡን ምንጮቹ ገልጸዋል፡፡

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የዳርፉር የሰላም አስከባሪ ጦር ዋና አዛዥ የነበረው ታደሰ ወረደ ምትክም ዮሀንስ የተባለው ተተክቶ ስራ የጀመረ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ለአንድ ተራ ክፍለ ጦር የብርጋዴየር ጄኔራል ማዕረግ ያላቸው አፍለኛ መኮንኖች እየተመደቡ መሆኑን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋልጠዋል፡፡

ሰሞኑን በተደረገ አዲስ ምደባ መሰረት ለሰሜን እዝ 21ኛ ክፍለ ጦር የኦህዴዱ የጦር አለቃ ድሪባ መኮንን የተመደበ ሲሆን በሌሎችም እዞች ውስጥ በሚገኙ ክፍለ ጦሮች አዳዲስ ብ/ጄ/ል ማዕረግ ያላቸው መኮንኖች መመደባቸውን ምንጮቹ አስረድተዋል፡፡

በኢትዮጵያ ዘመናዊ የጦር መዋቅር ስራ ከጀመረበት ግዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ የአንድ ክፍለ ጦር ዋና አዛዥ ሆኖ የሚመደበው የኮሎኔል ማዕረግ ያለው መኮንን የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት ወያኔ በምስጢር የሚሾማቸው ጄኔራሎች ቁጥር ወደ ሺህ የሚጠጋ በመሆኑ የሚመደቡበት ቦታ በመጥፋቱ ለክፍለ ጦር አዛዥነት እየተመደቡ መሆኑን ምንጮቹ ጨምረው ገልጸዋል፡፡

በወያኔው ኤታማዦር ሹሙ ሳሞራ የኑስ ፊርማ ነባር የሆኑት እየተሰናበቱ ለአዳዲስ አፍለኛ ጄኔራሎች ምደባ እየወጣላቸው ሲሆን አብዛኛዎቹ ወደ ክፍለ ጦር እና በየመምሪያው ውስጥ እየተመደቡ መሆናቸውን ምንጮቹ አክለው ገልጸዋል፡፡

ሰሞኑን የተደረገውን አዲስ ምደባን ተከትሎ ከደቡብ ሱዳን ጋር በተደረሰው ምስጢራዊ ወታደራዊ ስምምነት መሰረት የአየር እና የእግረኛ ቅኝት በተጨማሪ ታጣቂ የተቃዋሚ ኃይል አለበት ተብሎ በሚጠረጠሩ የደቡብ ሱዳን ግዛት ውስጥ ወያኔ አንድ ሻለቃ ጦር በምስጢር ያሰፈረ ሲሆን ይሄንን ጦር የሚመራው አንድ የጄኔራል ማዕረግ ያለው መኮንን መሆኑን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ አስረድተዋል፡፡